ዲሴምበር 17 ቀን 2006 ዓ/ም

ይድረስ ለዶ/ር ብርሃኑ ነጋ
ቃሊቲ ወህኒ ቤት
አዲስ አበባ

ውድ ዶ/ር ብርሃኑ

“የነፃነት ጎህ ሲቀድ“ የተሰኘውን መጽሐፍህን ያነበብኩት በስስትና ባድናቆት ስሜት ነው። አንድ አምስቱን ገጽ አነብና ወደፊት ከመቀጠል ይልቅ ተመልሼ ያንኑ አምስት ገጽ እደግመዋለሁ። አንድም መጽሐፉ እንዳያልቅብኝ ከመጓጓት፤ አንድም ደግሞ መልዕክትህን በቅጡ ከራሴ ጋር ለማዋሀድ ካለኝ ምኞት ነው።

ራስህን ነጻ ያወጣህ ሰው በመሆንህ ምንኛ ታድለሀል! መጽሐፍህ የተሞላው በሃቅ፤ በወገንና በሃገር ፍቅር፤ በአስታራቂነት፤ በአቻቻይነት፤ በሠላም ፈላጊነትና፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ በተስፋ ሰጭ ሃሳቦች ስለሆነ ዘመናት የማይሽሩት የታሪክ ቅርስ እንደሚሆን አልጠራጠርም። ግራና ቀኙን ያገናዘበው አስተዳደግህ ወደፊት ለመጓዝ ያሉንን አማራጮች በርቱዕ አመላከተን። ከንግዲህ ያዲሱን ትውልድ ሃላፊነት እንጅ ያለፈውን ትውልድ እዳ ማባዘቱ ፋይዳ እንደሌለው አሳየኸን። በብሔረሰብ ጥያቄ ላይ የተመሰረተው የግራ ፖለቲካ ስብስቴያዊ መሆኑን፤ የብሄረሰቦች ጥያቄ ከ1970-1990 የፖለቲካ ዘመን እስኪበቃው የተወያየንበትና ብሔራዊ እርቅ ያገኘንበት መሆኑን፤ ከ1990-2005 የፖለቲካ ዘመን ደግሞ ብሔራዊ እርቃችንን አጠናክረን ወደግንባታ የምናመራበት ዕድል ከፍቶልን እንደነበር አብራራህልን።

የኢሕአዴግ የፖለቲካ ርእዮት የሚያተኩረው ሊድን የተዳረሰውን የጎሳ ቁስል በመነካካት ሕዝባችን በቀድሞው የጥርጣሬ ህይወት ውስጥ እንዲኖር በማድረግ ላይ ነው። ይህ ሴራ ለምንና ለማን ሲባል እንደተጠነሰሰ የኢትዮጵያ ህዝብ ለማወቁ በ97ቱ ምርጫ ወቅት በካርዱ አማከይነት መስክሯል። የሴራው አጨብጫቢ ሆነው የቀሩት ከገዥው ፓርቲ ፍርፋሪ የሚጣልላቸው ጥቂት የህብረተሰብ አባላት ናቸው። እነርሱም ቢሆኑ በልባቸው ልብ ውነተኛው መንገድ የትኛው እንደሆነ ስለሚያውቁ ያሳዳሪወቻቸው ጀንበር ማቀልቀል ስትጀምር ወደሃቁ መንደር ይቀላቀላሉ። በራስህ መጽሃፍ ውስጥ እንዳመለከትከው ኢሕአዴግ ታማኝነትን በገንዘብና በሹመት ለመግዛት ያደረገው ከንቱ ሙከራ ኪሳራ እንጅ የምርጫ ካርድ እንዳላስገኘለት አይቶታል።

ውድ ዶ/ር ብርሃኑ፣

እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ስለወደፊቷ አትዮጵያ ሳላሰላስል የምታልፍ ቀን የለችም። ከሰሞኑ በዚህ በዋሽንግተን ዲሲ የፌስቲላ በሽተኞችን ለመርዳት በተዘጋጀ በዓል ላይ ተገኝቶ ያደረብኝን ትልቅ ተስፋ ላጫውትህ። የዝግጅቱ ጥራትና ያዘጋጆቹ የሙያ ደረጃ ሕብረተሰባችን የደረሰበትን የብቃት እርከን ግልጽ አርጎ የሚያመላክት ነበር። ርዳታ ለማድረግ የመጣውም ወገን ባብዛኛው ከፍተኛውን የትምህርት እርከን ያለፈ መሆኑ ከሩቁ ያስታውቃል። ታዲያ በማየውና በምሰማው እየፈነጠዝኩ እያለሁ አንድ ሃሳብ ይመላለስብኝ ጀመር። በዚያ አዳራሽ ከተሰበሰበው ብዙ መቶ ባለሙያ ውስጥ አንድ አሥረኛው እንኳ ዕውቀቱን ወደ ዲሞክራሲ፤ ወደ መብትና ወደ መልካም አስተዳደር የፖለቲካ ሥራ መለስ ቢያደርግ ትግላችን የት በደረሰ እያልኩ አሰላሰል ጀመር።

ችግሩ ለነዚህ ክቡር ዓላማወች ከቆሙና ወገንን ከኋላቀርነት ለማላቀቅ በሚያስችል የፖለቲካ ሥራ ውስጥ ከተሰማሩ ድርጅቶች ጋር መቀናጀትን ከእሳት ጋር እንደመጫወት አድርገን የምንቆጥር ብዙ መሆናችን ላይ ነው። በቀይ ሽብር፤ በነጭ ሽብርና በሌላ ዓይነት ሽብር በደነገጠ ሕብረተሰብ ውስጥ እንዲህ ዓይነት አመለካከት መኖሩ እጅጉን ሊያስገርም ባይገባም በነፃነትና በሠላም በምንኖርበት ባሜሪካና ባውሮፓ ውስጥ ይህን ፍርሃት አዝለን መኖራችን ግራ ያጋባኛል።

ሁሉም ሰው ለፖለቲካና ለማህበራዊ ፍትህ እኩል ይቆማል፤ እኩል ያዋጣል፤ እኩል ይሠለፋል፤ የሚል ጉጉት የለኝም። የሁላችንም አቅምና ግንዛቤ የየራሱ መነሻ ስላለው አስተዋጽኦችንና ተሳትፏችን ከዚያ ጋር የተመጣጠነ መሆኑን በፀጋ እቀበላለሁ።

ለዲሞክራሲ መቆምና ለመብት መታገል ተፈጥሮ ያደለንን ፀጋ እንደመንከባከብ ሊቆጠር ይገባል። ለነዚህ የተፈጥሮ ፀጋዎች የምናደርገው እንክብካቤም ልጆቻችንንና ንብርታችንን ከክፉ ለመጠበቅ ከምናደርገው እንክብካቤ ማነስ የለበትም እላለሁ። ማሃተመ ጋንዲ፤ ኔልሰን ማንደላ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግና ሮዛ ፓርክ ፍትህና መብት በታፈኑበት ህብረተሰብ ውስጥ መኖርን አንቀበልም ብለው ለየራሳቸው ያደረጉት ትግል ለሁላችንም መድህን ሆነ።

ማህበረሰብን ነፃ የሚያወጣው የሮዛ ፓርኮች የጥረትና የተሳትፎ ድምር ስለሆነ መቀመጫችንን አንለቅም ማለትን መልመድ አለብን።

ዲሞክራሲንና ፍትህን ለማስፈን በሚደረግ ትግል ውስጥ የምናዋጣው አንድ ሰዓትም ሆነ አንድ ብር ትልቅ ቁምነገር እንደሚሠራና የህሊና ርካታ እንደሚሰጥ ልናውቅ ይገባል። ቀድም እንዳልኩት ቁምነገሩ ያለው ከገንዘቡና ከተሳትፏችን ብዛት ላይ አይደለም። በትንሿም ብትሆን ከመሳተፋችን ላይ እንጅ።

ውድ ዶክተር ብርሃኑ!

ወደምርጫ 97 በሚወስደው ጎዳና ላይ በየቦታው እየተዘዋወርክ ገለጻ በምታደርግበት ወቅት ለብዙዎቻችን ያስጨበጥከው ቁምነገር ከቶውንም አይዘነጋኝም። "ፖለቲካ ውስጥ ልገባ የወሰንኩት ግዙፍ ዓላማ አንግቤ ሳይሆን ዲሞክራሲንና ፍትህን ዕውን ለማድረግ በሚደረግ ጥረት ውስጥ የበኩሌን አስተዋጻኦ ማድረግ አለብኝ ከሚል ግንዛቤ ላይ ለመድረስ በመቻሌ ነው" ብለህ ነበር። "የታዳጊ ልጆቼና የልጅልጆቼ ተወቃሽ መሆንን ስላልፈለግሁ ነው" ብለህ ነበር።

ይህ አባባልህ ከዲሞክራሲና ከመብት ትግል ውጭ የነበርነውን ብዙ ወገኖችህን ወደመሃል እንድንመጣ ረድቶናልና ምስጋና ይግባህ። ከሞቀና ከደመቀ ቤታችሁ ወጥታችሁ በቃሊቲ እሥር ቤት መሆናችሁ ለናንተም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሞራል የበላይነቱን አጎናጸፋችሁ። አሳሪዎቻችሁ ግን ያተረፉት ውድቀትንና ጸጸትን ነው።

"የነፃነት ጎህ ሲቀድ" የተሰኘው መጽሓፍህ ባሳሪዎችህ ላይ የተጎናጸፍከውን የህሊና የበላይነት እጅጉን አድምቆ ያሳያል።

ውድ ዶ/ር ብርሃኑ!

አንተም ሆንክ አብረውህ ያሉ የዲሞክራሲ ታጋዮች እራሳችሁን ነፃ ያወጣችሁ በመሆናችሁ ምንኛ ታድላችኋል!

ካክብሮት ጋር
ኩችዬ